# የፍጆታ አገልግሎትዎን መልሰው መግኘት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

ነዋሪዎች አገልግሎታቸው ከጠፋ በኋላ ኤሌክትሪካቸውን፣ ጋዝ፣ እና/ወይም ዘይት መልሰው ለማግኘት የድንገተኛ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። አገልግሎቶች የመጥፋት አደጋ ውስጥ ካሉ በእድሜ ጠና ያሉ ግለሰቦች እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። እኛ— የዲሲ መንግስት—**እስከ $600** የሚሆን ገንዘብ ለ PEPCO፣ Washington Gas እና/ወይም ለDC Oil ጊዜያቸው ያለፉባቸው ሂሳቦችን ክፍያ እናቀርባለን።

ፕሮግራሙ Emergency Low Income Home Energy Assistance Program (LIHEAP፣ የድንገተኛ የዝቅተኛ ገቢ የቤት ሃይል ድጋፍ ፕሮግራም) በመባል ሲታወቅ በ Department of Energy and Environment (በኢነርጂና አካባቢ መምሪያ) ይቀርባል።

## ብቁ መሆንዎን ያጣሩ።

እነዚህ መግለጫዎች **በሙሉ** እውነት ከሆኑ፣ ብቁ ነዎት ማለት ነው፡

- ቤትዎ ዲሲ ውስጥ ከሆነ።
- ኤሌክትሪክ ወይም ጋዝ ጠፍቶ ከቆየ ወይም የእርስዎ የዘይት ማከማቻዎ ከ 5% በታች ከሞላ። 55 አመትና ከዛ በላይ ከሆኑ፣ አገልግሎትዎ አሁንም ድረስ የሚሰራ ይሁን እንጂ ጊዜው ያለፈበትን ሂሳብ ካልከፈሉ አገልግሎቱ የሚቋረጥ ከሆነ እርስዎ ብቁ ነዎት።
- የእርስዎ ስም ወይም በቤተሰብዎ ውስጥ ያለ የሆነ ሰው ስም፣ ፍጆታ ክፍያዎ ላይ ከተዘረዘረ። ይህ ካልሆነ፣ በቤትዎ ውስጥ ያለ የሆነ ሰው የቤቱ ባለቤት መሆኑን ማሳየት አለብዎት ወይም የእርስዎን የፍጆታ ክፍያ ለመክፈል ሃላፊነቱን የወሰደ መሆን አለበት።
- እንዲሁም ከእነዚህ ውስጥ **አንዱ** ትክክል ከሆነ፡

- ቤተሰብዎ ከሚከተሉት ፕሮግራሞች ቢያንስ በአንዱ ድጋፊ የሚያገኝ ከሆነ፡ ተጨማሪ የምግብ ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP)፣ ጊዜያዊ ድጋፍ ለሚፈልጉ ቤተሰቦች (TANF) ወይም ተጨማሪ የደህንነት ገቢ (SSI)***ወይም***

- የቤተሰብዎ አመታዊ አጠቃላይ ገቢ —ግብርን ከመክፈልዎ በፊት ያለው የእርስዎ ገቢ— በቤተሰብዎ መጠን ላይ ተመስርቶ ከገደቦቹ እኩል ወይም በታች ነው። ገቢዎን ለማስላት፣ አብረው ስራ በመስራት ገቢ የሚያገኙትን አዋቂ ሰዎች ገንዘብ ይደምሩ፡፡ ከዚያ፣ ከ 18 አመት በታች ያሉትን ልጆች አጠቃልሎ ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውም ሰው ከማህበራዊ ዋስትና፣ ከስራ አጥነት፣ ከልጅ ድጋፍ ወይም የጡረታ ክፍያዎች የሚያገኘውን ገንዘብ ይደምሩ። ከዚህ በታች ምልክት ያኑሩ።

| **የቤተሰብ መጠን** (ከእርስዎ ጋር የሚኖር ማንኛውንም ሰው ይቁጠሩ) | **ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ** |
|---|---|
| 1 | $37,575 |
| 2 | $49,137 |
| 3 | $60,698 |
| 4 | $72,260 |
| 5 | $83,822 |
| 6 | $95,383 |
| 7 | $97,551 |
| 8 | $99,719 |

## ያመልክቱ።

1. **ለእርስዎና በቤተሰብዎ ውስጥ ለሚኖር ለእያንዳንዱ ሰው** የሚከተሉትን መረጃዎች ይሰብስቡ። ቢያንስ በአንዱ ሰነድዎ ውስጥ የእርስዎ ሙሉ ስም መዘርዘር አለበት እንዲሁም እርስዎ በዲሲ ውስጥ እንደሚኖሩ ለማሳየት የዲሲ አድራሻ መኖር አለበት። እንዴት እንደሚያመለክቱ ባለው ሁኔታ ላይ ተመስርቶ፣ ሰነዶችዎን ቅጂ ማድረግ ወይም ስካን ማድረግ ሊያስፈልግዎ ይችላል።

    - ፎቶ ያለባቸው መታወቂያዎች (ልክ እንደ መንጃ ፈቃድ ያሉ)
    - የማህበራዊ ዋስትና ካርዶች ወይም የውጭ ዜጋ ምዝገባ ቁጥሮች
    - ለተቋረጡ ፍጆታ ወይም ፍጆታዎች በጣም የቅርብ ጊዜ የፍጆታ ክፍያ
    - የቅርብ ጊዜ የክፍያ ደረሰኞች፣ የማህበራዊ ዋስትና መግለጫዎች፣ የጡረታ መግለጫዎች፣ የስራ አጥ ጥቅማ ጥቅም መግለጫዎች፣ የልጅ ድጋፍ መግለጫዎች፣ እና/ወይም የታክስ ተመላሾች (ለእርስዎ የሚሆን ሁኔታ ጋር የሚተገበሩ ሰነዶች ብቻ ያስፈልጉዎታል)

    - ከ PEPCO እና/ወይም ከWashington Gas ኤሌክትሪክዎ እንደጠፋ የሚያሳይ ደብዳቤ። 55 አመትና ከዚያ በላይ ከሆኑ፣ የኤሌክትሪክ ወይም የጋዝ አገልግሎት እንደሚቆም ብቻ የሚያሳይ ደብዳቤ ያስፈልግዎታል። የዘይት ማከማቻዎ 5% እና ከዚያ በታች ከሆነ፣ የቀረዎት ምን ያህል እንደሆነ ለእኛ መንገር ያስፈልግዎታል።

2. በኦንላይን ወይም በፖስታ መልእክት ለማመልከት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ይምረጡ፡

    - [የኦንላይን ማመልከቻውን](#) ይሙሉ። ለመጀመር በመለያ መግቢያ እንዲፈጥሩ ይጠየቃሉ። ለዝቅተኛ ገቢ የቤት ሃይል ድጋፍ ፕሮግራም (Low Income Home Energy Assistance Program) እና የፍጆታ ቅናሽ ፕሮግራም (Utility Discount Program) ላይ ፍላጎት እንዳለዎ ይምረጡ። የሰነዶችዎን ፎቶዎች ወይም ስካኖች ወደ ማመልከቻው እንዲሰቅሉ ያስፈልጋል።

    - በፖስታ መልእክት ለማመልከት፣ ከዶክመንቶችዎ ቅጂዎች ጋር አንድ ላይ በማድረግ ያጠናቀቁትን [የወረቀት ማመልከቻ](#) ፕሪንት አድርጎ ከዚህ በታች በተቀመጠው አድረሻ በኩል መላክ። ማመልከቻውን ፕሪንት ማድረግ የማይችሉ ከሆነ፣ በማንኛውም ሰዓት በ311 ላይ በመደወል ማመልከቻዎን

እንድንልክልዎት ሊጠይቁን ይችላሉ። ሰነዶችዎን ቅጂ ማድረግ ይኖርብዎታል። እባክዎን ዋናውን ሰነዶች አይላኩ።

Attn: Emergency LIHEAP
The Department of Energy & Environment
810 1st Street NE, 9th Floor
Washington, DC 20002

በማንኛውም ጊዜ ማመልከት ይችላሉ።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

# ካመለከትኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?

1. ባመለከቱ በሁለት ቀናት ውስጥ እኛ —የዲሲ መንግስት—እርስዎ ተቀባይነት ካገኙ በስልክ ወይም በኢሜይል እንነግርዎታለን። በተጨማሪም በማመልከቻው ዙሪያ አዲስ ነገር እንዳለ ለማወቅ፣ በ311 ላይ መደወል ይችላሉ።

2. እኛ **እስከ $600** የሚሆን ገንዘብ ለ PEPCO፣ Washington Gas እና/ወይም ለ DC Oil ጊዜያቸው ያለፉባቸው ሂሳቦችን እናቀርባለን። ከአንድ በላይ የሆኑ ፍጆታዎችዎ ከቆሙ፣ አገልግሎትዎ እንዲመለስ እስከ $600 ለእያንዳንዱ ፍጆታ እንከፍላለን። 55 አመትና ከዛ በላይ ከሆኑ፣ አገልግሎትዎ አሁንም ድረስ የሚሰራ ከሆነና ነገር ግን ያልተከፈለ ሂሳብ ካልከፈሉ አገልግሎቱ የሚቋረጥ ከሆነ እርስዎ ብቁ ነዎት።

3. ለአስቸኳይ ድጋፍ ከተፈቀደልዎ በኋላ በሂሳብዎ ላይ ያለውን የስልክ ቁጥር በመጠቀም ወደ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያው በመደወል አገልግሎትዎን እንዲያበሩ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ የፍጆታ ድርጅቱ ብዙውን ጊዜ ከደወሉ በኋላ አገልግሎትዎን በአንድ የስራ ቀን ውስጥ መልሶ እንዲያሰራ ያደርጉታል። $600 ጊዜው ያለፈበትን ያልተከፈሉ ክፍያዎችን ለመሸፈን የማይበቃ ከሆነ፣ አገልግሎትዎን መልሰው ከመጀመርዎ በፊት ልዩነቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሸፍኑ ሊጠይቅዎት ይችላሉ።

4. አስቸኳይ ያልሆኑ የፍጆታ ድጋፎችን ከእኛ ቀድመው ካላገኙ፣ ለምን ያህል ድጋፍ ብቁ እንደሆኑ በአካል ወይም በኢሜይል እናሳውቅዎታለን እንዲሁም ወደፊት ለሚመጡት የፍጆታ ክፍያዎች ወዲያው ድጋፍ እንዲያገኙ እንመዘግብዎታለን። ማመልከቻ ካቀረቡበት ጊዜ አንስቶ በሁለት የሂሳብ አከፋፈል ዙሮች ውስጥ (ከሁለት

ወር በኋላ) በሂሳብዎ ላይ ያሉትን ክሬዲቶች እና/ወይም ቅናሾች መመልከት ይጀምራሉ።

ተቀባይነት ካላገኙ፣ በስልክ ወይም በኢሜይል ካመለከቱበት ቀን በኋላ ባሉት በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን። በተጨማሪም በማመልከቻው ዙሪያ አዲስ ነገር እንዳለ ለማወቅ፣ በ311 ላይ መደወል ይችላሉ። ማመልከቻዎ ተቀባይነት እንዳላገኘ በሰሙ በ 90 ቀናት ውስጥ በውሳኔያችን ላይ ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ። ስምዎን፣ አድራሻዎን እንዲሁም እርስዎን ማግኘት የምንችልበት የተሻለውን መንገድ (በስልክ ወይም ኢሜይል) ብቻ እንፈልጋለን። በኦንላይን ወይም በ 311 ላይ በመደወል ወይም ወደእኛ በሚከተለው አድራሻ በመጻፍ ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

Office of Administrative Hearings
441 4th Street, N.W., Suite 450 North
Washington, D.C. 20019

## ሁሉም ብቁ አመልካቾች የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ያገኛሉ?

አዎ።

## ማወቅ ያለብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

የፍጆታ ሂሳብዎ ስምዎን ወይም በቤትዎ ውስጥ የሌላውን ሰው ስም የማይዘረዝር ከሆነ፣ ከቤተሰብዎ ውስጥ ያለ ሰው የቤትዎ ባለቤት እንደሆነ ወይም የፍጆታ ሂሳብዎን የመክፈል ኃላፊነት እንደወሰደ ማሳየት መቻል አለብዎት።

## ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

መጀመሪያ በገጹ የታችኛው ላይ የሚገኘውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ። አሁንም ድረስ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ በ311 ላይ በማንኛውም ጊዜ ደውለው ያግኙን። ወይም በ liheap.support@dc.gov ላይ በርዕሰ መስመር “Emergency LIHEAP Question” በሚል ኢሜይል ሊያደርጉልን ይችላሉ።

## በፍጆታዎቼ ላይ አሁንም እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?

በእኛ የፍጆታ ሀብቶች ገጽ ላይ ስለሌላ እርስዎን ሊረዱ ስለሚችሉ መረጃዎች ማግኘት ይችላሉ።

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ከሌሎች የሃይል ድጋፎችና የቀልጣፋነት ፕሮግራሞች ጋር ይህንን ፕሮግራም ማጣመር እችላለሁ?

አዎ። ለአስቸኳይ ድጋፍ ሲያመለክቱ፣ ለኤሌክትሪክ፣ ጋዝ፣ ዘይትና የውሃ ክፍያዎች ድጋፍ ክፍያ ብቁ መሆንዎን ወዲያውኑ እናረጋግጣለን። ፍጆታዎን እንደገና ለመጠቀም ለአስቸኳይ ድጋፍ ፈቃድ ካገኙ፣ ማመልከቻዎን ባስገቡበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት የሂሳብ አከፋፈል ዞሮች ውስጥ (ከሁለት ወር በኋላ አካባቢ) በሂሳብዎ ላይ ያሉ ክሬዲቶች እና/ወይም ቅናሾችን ማየት ይጀምራሉ።

የቤትዎን ሙቀትና ኤሌክትሪክ አጠቃቀም ለመቀነስ እንዲሁም/ወይም የተበላሸ ማሞቂያ ወይም ማቀዝቀዣ መሳሪያ ለመተካት እርዳታ ማግኘት እንደሚፈልጉ በተጨማሪ መናገር ይችላሉ። ፍጆታዎን እንደገና ለመጠቀም ለአስቸኳይ ድጋፍ ፈቃድ ካገኙ፣ ለእነዚህ ፕሮግራሞች እንዴት እንደሚያመለክቱ በመግለጽ በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ኢሜይል እናደርግልዎታለን።

## ምን ያህል የአስቸኳይ ድጋፍ እንደምቀበል የሚወስነው ምንድን ነው?

የድጋፍ መጠኑ **እስከ $600** ድረስ ሊሆን ይችላል። የሚቀበሉት መጠን የሚመሰረተው በቆመው ፍጆታ ምን ያህል እዳ እንዳለብዎ ሲታወቅ ነው። ከአንድ በላይ የሆኑ ፍጆታዎ ከቆሙ፣ አገልግሎትዎን ለመመለስ እስከ $600 የሚሆን መጠን ለእያንዳንዱ ፍጆታ እንከፍላለን። 55 አመትና ከዛ በላይ ከሆኑና ከአንድ በላይ የሆኑ ፍጆታዎ የመቆም አደጋ ውስጥ ካሉ፣ አገልግሎትዎን ለማስቀጠል እስከ $600 ለእያንዳንዱ ፍጆታ እንከፍላለን።

## ከፕሮግራሙ ከዚህ ቀደም ድጋፍ አግኝቼ ብሆን የአስቸኳይ ድጋፍ ማግኘት እችላለሁ?

አዎ፣ የብቁነት መስፈርቱን አሟልተው እስከሚገኙበት ጊዜ ድረስ የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ እንደገና ሊያገኙ ይችላሉ ነገር ግን ከኦክቶበር ጀምሮ ሴፕቴምበር ላይ በሚያበቃው በጀት አመት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ይቀበላሉ። ለምሳሌ፣ በዚህ ዓመት ኖቬምበር ላይ የአስቸኳይ ድጋፍ ከተቀበሉ፣ እስከሚቀጥለው አመት ኦክቶበር ድረስ እንደገና አይቀበሉም።

## ሁለትና ከዚያ በሆኑ የተለያዩ የፍጆታ ክፍያዎች የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ ማግኘት እችላለሁ?

አዎ። ከአንድ በላይ የሆኑ ፍጆታዎችዎ ከቆሙ፣ አገልግሎትዎን ለመመለስ ለእያንዳንዱ እስከ $600 እንከፍላለን። 55 አመትና ከዛ በላይ ከሆኑና ከአንድ በላይ ፍጆታዎ የመቆም አደጋ ውስጥ ከሆነ፣ አገልግሎትዎን ለመመለስ እስከ $600 የሚሆን እንከፍልልዎታለን።

## የእኔ የፍጆታ ክፍያዬ ቤቴ ውስጥ በሚኖር በማንኛውም ሰው ስም አይደለም። አሁንም ማመልከት እችላለሁ?

አዎን፣ አሁንም ድረስ ማመልከት ይችላሉ። የእርስዎ PEPCO፣ Washington Gas ወይም DC Oil የቤተሰብ አባልን ስም የማይዘረዝር ከሆነ፣ ከቤተሰብዎ ውስጥ የሆነ ሰው የቤትዎ ባለቤት እንደሆነ የሚያሳይ ወይም የኪራይ ውል ቅጂ ከቤተሰብዎ ውስጥ ያለ ሰው ለ PEPCO፣ Washington Gas ወይም DC Oil ክፍያዎች ሃላፊነቱን እንደወሰደ የሚገልጽ ማረጋገጫ ማከትት አለብዎት።

## ቤተሰቤ ምንም አይነት ገቢ የለውም። ያንን እንዴት ላረጋግጥ እችላለሁ?

ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ የሌለው ከሆነ፣ ከማመልከቻዎ ጋር **ከእነዚህ ውስጥ አንዱን ሰነድ ማስገባት** ይችላሉ፡

- በውል አዋዋይ ባለስልጣን የተረጋገጠ የገቢ መግለጫ፣

- Department of Employment Services (DOES፣ በቅጥር አገልግሎቶች ክፍል) ድረ ገጽ “ቀሪ ሂሳብዎ” ዜሮ እንደሆነ የሚያሳይ የእርስዎ “ይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ መገለጫ” ቅጽበታዊ ገጽ እይታ (ምሳሌውን ይመልከቱ)፣
- ከቀድሞ አሠሪዎ የተጻፈና ከአሁን በኋላ እዛ እንደማይሠሩ የሚገልጽ ደብዳቤ (ከስራ ከለቀቁ ግን እስካሁን ድረስ የሥራ አጥነት ጥቅሞችን በ DOES እያገኙ ካልሆነ)፣ **ወይም**
- ከ District of Columbia Housing Authority (DCHA፣ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት የመኖሪያ ቤት ባለስልጣን) የመጣው ደብዳቤ የሚገልጸው ቤተሰብዎ ምንም አይነት ገቢ እንደሌለው ነው።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*